የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፩

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.15
ADDIS ABABA 25th December, 2018

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፬፻፵፪/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የውሃ ልማት ኮሚሽንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………………..…………………ገጽ ፲ሺ፯፻፹፬

**Content**

Regulation No. 442/2018

Definition of Power, Duties and Organization of the Water Development Commission Council of Ministers Regulation.--.........................Page 10784

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፪/፪ሺ፲፩

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 442/2018

**የውሃ ልማት ኮሚሽንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE THE DEFINTION OF POWER, DUTIES AND ORGANZATION OF THE WATER DEVELOPMENT COMMISSION**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

This Regulation is issued by the Councils of Ministers pursuant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/ 2018.

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የውሃ ልማት ኮሚሽንን ሥልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፪/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Definition of Power, Duties and Organization of the Water Development Commission Council of Ministers Regulation No. 442/2018"

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፡-

፩/ **"የውሃ ልማት "** ማለት የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ልማት ነው፤

፪/ **"ንፁህ መጠጥ ውሃ"** ማለት የኢትዮጵያ የመጠጥ ውሃ የጥራት ደረጃን ያሟላ ውሃ ነው፤

**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Water Development" means the development of potable water and sanitation ;

2/ "Potable water" means water that meet the Ethiopian drinking water quality standards;

፫/ **“ሳኒቴሽን አገልግሎት”** ማለት ማናቸውንም ከቤትና ከተለያዩ ተቋማት የሚወጣውን ፍሳሽ በተገቢው መንገድ መሰብሰብ፣ ማስወገድና ማስተዳደርን ያካትታል፣

፬/ **“ፍሳሽ“** ማለት ከመኖሪያቤት፣ከፋብሪካና ከሌሎችም ቦታዎች ተበክሎ የሚወጣ ፈሳሽ ነው፣

፭/ **“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር“** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የውሃ፣መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

፮/ **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፣

፯/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## ፫. ዋና መሥሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## ፬. የኮሚሽኑ ዓላማ

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በሃገሪቱ ጤናማና አምራች ዜጋ ለመፍጠር እንዲሁም ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት የሚያስችል ዘላቂና አስተማማኝ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ሽፋን ማሳደግ፣

፪/ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት አስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ የሃገሪቱን የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል፡፡

## ፭. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በከተማና በገጠር የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችሉ የጥናትና ዲዛይን ሥራዎችን ያከናውናል፣ ያስተባብራል፣

፪/ በከተማና በገጠር የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችሉ የመሰረተ ልማቶችን ክልሎችን በመደገፍ ያከናውናል፣

3/ “Sanitation service” means safe and sustainable collection, removal and management of domestic and institutional liquid wastes;

4/ “Sewage” means liquid effluents discharged from domestic, industrial and other sources;

5/ “Ministry” or “Minister” means the Ministry or the Minister of Water, Irrigation and Energy, respectively;

6/ “Regional State” means any State referred to under article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administration ;

7/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Head Office

The Commission shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

## 4. Objectives

The commission shall have the following objectives:

1/ create healthy and productive citizen and bring rapid and sustainable economic development by increasing the coverage of potable water supply, sanitation and hygiene through carrying out the study, design and construction of sustainable potable and reliable water supply and sanitation infrastructure;

2/ Improve the nation’s potable water supply and sanitation service management through implementation of improved water supply and sanitation service delivery system.

## 5. Power and Duties of the Commission

The commission shall have the following powers and duties:

1/ Coordinate and conduct potable water supply and sanitation infrastructure study and designs in rural and urban areas;

2/ Provide support to the regions for infrastructure development of potable water supply and sanitation services in urban and rural areas;

፫/ የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ተቋማት ግንባታ በወጪ ማስመለስ እና በፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፤

፬/ ከፌደራል መንግስት በጀትና ከውጪ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ግንባታዎች በጥናትና ዲዛይናቸው መሠረት የጥራት ደረጃውን ጠብቀው መከናወናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፭/ ሃገራዊ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን የጥናትና ዲዛይን፣ የግንባታና የተቋማት አስተዳደር መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶችና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፮/ ሃገራዊ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ያሰራጫል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፤

፯/ የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፤

፰/ ለንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ሥራዎች የሚውል ተጨማሪ ፋይናንስ ከባለድርሻ አካላት፣ ከለጋሾች እና ከአጋሮች ያፈላልጋል፤

፱/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለመጠጥ ውሃ ግልጋሎት የሚውል ውሃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ አጥንቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

፲/ በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ በአገልግሎት ሰጪነት፣ በአማካሪነት፣ በሥራ ተቋራጭነት፣ በምርትና ዕቃ አቅርቦት የተሰማሩ የግል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን አቅም ለመገንባት የሚያስችል ድጋፍ የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፩/ በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይሰራል፤

፲፪/ በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ወገኖች ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይሰራል፤

፲፫/ በውሃና ሳኒቴሽን ጥናትና ዲዛይን፣ ግንባታ፣ ኦፕሬሽንና ጥገና እንዲሁም ተቋማት አስተዳደር ሥራ ላይ ወጣቶችና የግሉ ዘርፍ ተሳታፊ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋል፤

3/ Ensures potable water supply and sanitation development to be based on the principle of cost recovery and equitable use;

4/ Follow up and monitor potable water supply and sanitation infrastructure development projects study, design and construction financed by the federal government and loans and grants from abroad are in line with the national design quality standard;

5/ Prepare , disseminate and follow up the implementation of national potable water supply and sanitation study , design, construction and utility management criteria, guideline, standards and manual ;

6/ Develop, analyze, disseminate and update the national water supply and sanitation database system;

7/ Provide support to raise the potable water supply and sanitation infrastructure coverage;

8/ Secure additional financial resources from stakeholders, donors and development partners to potable water and sanitation works;

9/ In collaboration with appropriate stakeholders, studies quality standards that potable water shall have and submit to the ministry;

10/ Facilitate ways in which capacity building supports are given to service providers, consultants, contractors and private, governmental and non-governmental organizations involved with material providing in potable water supply and sanitation sector;

11/ Ensure the participation and benefits of women in the potable water supply and sanitation development;

12/ Ensures the benefits of groups that need special support in the potable water supply and sanitation development;

13/ Provide support to youth and private sector so that they can involve in the study design, construction, operation and maintenance as well as management of water supply and sanitation;

፲፬/ የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሥራን በማስፋት በተለይ በውሃ-አጠር አካባቢዎች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችና እንስሳትን ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፲፭/ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ልማቶች አካባቢያዊና ማህበራዊ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳያስከትሉ እንዲሁም የታከመ ፍሳሽና ተረፈ-ውጤቶችን መልሶ መጠቀም እንዲቻል ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፤ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤

፲፮/ በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሠረተ-ልማት ሥራዎች ላይ በየደረጃው የተጠቃሚው ህብረተሰብ ተሳትፎ መኖሩን ያረጋግጣል፤

፲፯/ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ተቋማት አዋጪ የሆኑ የታዳሽ ኢነርጂ አማራጮችን በመጠቀም አስተማማኝ አገልግሎት እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፰/ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የተቀናጀ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ የአስቸኳይ ጊዜ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፱/ ሃገራዊ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፳/ የዘርፉን የማስፈፀም አቅም የሚያሳድጉ ተግባራትን ያቅዳል፤ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳፩/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል ይከሰሳል፤

፳፪/ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ፡፡

## ፮. የኮሚሽኑ አቋም

ኮሚሽኑ፡-

፩/ በመንግስት የሚሾሙ ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነሮች፤ እና

፪/ አስፈላጊው ሰራተኞች

ይኖሩታል ፡፡

## ፯. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡

14/ Ensures access to potable water supply, particularly to communities and livestock in drought prone areas through promotion of climate resilient water supply strategy;

15/set the relevant system and follow up mechanism to mitigate adverse environmental and social impacts of water supply and sanitation projects and promote recycling of treated waste water and resources recovery.

16/ Ensures the participation of beneficiary communities in the implementation of water supply and sanitation infrastructures;

17/ Create enabling ground for the reliable service provision of water supply and sanitation schemes through the utilization of feasible alternative renewable energy resources;

18/ Provide integrated professional support to regions that seek special support; in coordination with relevant stakeholders provide support for emergency potable water supply and sanitation services;

19/ Prepare long, medium and short term national plan for potable water supply and sanitation sector and follow up its implementation;

20/ Plan activities that enhance the implementation capacity of the sector; suggest policy ideas and implement when approved;

21/ own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

22/ Implement other necessary duties which are required to achieve its goals

## 6. Organization of the Commission

The Commission shall have:

1/ A Commissioner and Deputy Commissioners, to be appointed by the government ; and

2/ the necessary staff.

## 7. Power and Duties of the Commissioner

1/ The Commissioner shall be the chief executive officer of the Commission and shall direct and administer the activities of the Commission.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኮሚሽኑን ሰራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ)የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ይተገብራል፤

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ)ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤

ረ) የኮሚሽኑን የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

፫/ ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የኮሚሽኑ የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፰. የምክትል ኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ኮሚሽነሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የኮሚሽኑን ተግባራት በማቀድ ፣ በማደራጀት ፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ያግዛል፤

፪/ በኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡ የስራ ዘርፎች ያከናውናል፤

፫/ ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሰራል፡፡

## ፱. በጀት

የኮሚሽኑ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

## ፲. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግባት ይይዛል፡፡

፪/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ሂሳብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

2/ without prejudice to sub-article (1) of this Article, the Commissioner shall;

a) exercise the power and duties of the commission specified under article 5 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Commission in accordance with the federal civil service laws;

c) prepare annual work plans and budgets of the Commission and implement the same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Commission;

f) represent the Commission in all its dealings with third parties;

g) submit to the Ministry performance and reports of the Commission.

3/ The Commissioner may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Commission to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Commission.

## 8. Power and Duties of Deputy Commissioner

The Deputy Commissioner shall have the following powers and duties:

1/ Assists the Commissioner in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the commission;

2/ perform duties specifically assigned to him by the Commissioner;

3/ Act on behalf of the Commissioner on his absence.

## 9. Budget

The Commission's budget shall be allocated by the Government.

## 10. Books of Accounts

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The book of accounts and financial documents of the Commission shall be audited annually by the Auditor General or an Auditor designated by him.

**፲፩. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ህዳር ፭ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**11. Effective Date**

This Regulation shall come into force on this 14th day of November, 2018, approved by the Council of Ministers.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of December, 2018.**

**ABIY AHIMED (PHD)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRACTICREPUBLIC OF ETHIOPIA**